በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

መንፈሳዊ ድራማ

"የተፈተነ ህይወት"

የዚህ መንፈሳዊ ተውኔት ዓላማ በሚገጥመን ነገር ሁሉ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብን

ወ/ሮ አገሬ የሶስና እና የዳዊት እናት ስትሆን ወ/ሮ አሰገደች ደግሞ የወ/ሮ አገሬ እህት የአቤል እናት ናት

ገብረ ጻድቅና ወለተ ማርያም ባልና ሚስት ናቸው ንስሓ አባታቸው ደግሞ አባ ኪዳነ ማርያም ናቸው።

ትዕይንት አንድ

መጋረጃ ሲከፈት ወ/ሮ አገሬ ሶስና እና ዳዊት ተቀምጠው ይታያሉ/

ወ/ሮ አገሬ፡-/ታማ ተኝታ /ሶስና ልጄ ዳዊትን አደራ ልጄ ከዚህ በኋላ ለዳዊት ያለሽው አንች ብቻ ነሽ አደራ--- አደራ--አደራ --ልጄ ዳዊትም ሶስናን እንዳታስከፋት /እያቃሰተች/

ሶስና፡-እናቴ አትሞችም አንች ከሌለሽ ማን አለን ደግሞ እንደምታይኝ ህጻን ነኝ ዳዊትም ማየት የተሳነው ነው ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ጥለሽን አትሞችም እማ እግዚአብሔር ይፈውስሻል አይዞሽ እናቴ እማ /እናቷን ደገፍ አድረጋ በማልቀስ/

ዳዊት ፡-እማ አትሞችም አይዞሽ እባክሽ አትጨነቂ እኛ እኮ ይከፋናል ያላንች ማን አለን እግዚአብሔር ይፈውስሻል

ወ/ሮ አገሬ፡-አታልቅሱ ልጆቼ ሞት እኮ ለሁሉም አይቀርም ይልቅስ ማለቀሱን ተውትና ነፍሴ የዘለዓለም ሞት እንዳያገኛት ጸልዩልኝ። ልጆች ተከባብራቹህ ኑሩ ሰውን ሁሉ አክብሩ ከእግዚአብሔር ቤት እንዳትለዩ አደራችሁን ልጆቼ /ወ/ሮ አሰገደች ትገባለች/

ወ/ሮ አሰገደች፡-ስላም ለዚህ ቤት ይሁን

ሶስና፡-እግዚአብሔር ይመስገን አክስቴ እንዴት ዋልሽ! ቁጭ በይ

ወ/ሮ አሰገደች፡-እንደምን ዋልሽ እህቴ ቀለል ብሎሽ ዋለ /በራስጌዋ በመቀመጥ/

ወ/ሮ አገሬ፡-እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ እኅቴ በመጣች እያልኩ ሳስብ መጣሽልኝ
ወ/ሮ አሰገደች፡-አይ እኅቴ ብመጣ ምን አደርግልሻለሁ እንደው ዓይንሽን ልየው ብየ ነው እንጅ ህመሙን አላግዝሽ
ዳዊት፡-አክስቴ እንኳን ደህና መጣሽልን እናታችን ስታስጨንቀን ነበር
ሶስና፡-አዎ ስታስጨንቀን ነበር አሁን አንች ስለመጣሽ እናቴ የተሻላት መሰለኝ
ወ/ሮ አሰገደች፡-አይዞአችሁ ደግሞ ዓይናችሁ አብጧል ስታለቅሱ ነው እንዴ የቆያችሁ ሰው እኮ ታሞ ይድናል እግዚአብሔር ይፈውሳል እናም አታስቡ ልጆች አንችም አታስጨንቂያቸው በርታ በርታ በይ እንጅ አትሞችም ምግብም ብይ እንድትጠነክሪ መመገብ አለብሽ /ድግፍ አድርጋ ይዛ/
ወ/ሮ አገሬ፡-እኅቴ አድምጭኝ እነዚህን ልጆች ለአንች አደራ እሰጥሻለሁ እናም እኅቴ ሞቴ እየተቃረበ ነው ልጆቼን እንደልጆችሽ አድርገሽ አሳድጊልኝ ። ከዚህ በኋላ እናታቸውም አባታቸውም አንች ነሽ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆች አድርጊልኝ አደራ --አደራ--!
ወ/ሮ አሰገደች፡-አገሬ ልጆችንማ የምታሳድጊያቸው አንች ነሽ አሁን ትድኛለሽ ብቻ አንች በርታ በርታ ማለት አለብሽ
ወ/ሮ አገሬ፡-አሰገደች አደራየንማ ተቀበይ ሶስናንና ዳዊትን አሳድጊልኝ። እህቴ ትሰሚያለሽ ልጆቼን በፈሪሀ እግዚአብሔር እንዳሳደኳቸው ከእንግዲህ አንችም በስርዓት አድገው አንችን አገርን የሚጠቅሙ ለቤተ ክርስቲያን አለሁ ልጅሽ የሚሉ አድርጊያቸው /በመተኛት / ከእንግዲህ ወደ እግዚአብሔር እሔዳለሁ /ትሞታለች/
ሶስና እና ዳዊት ወ/ሮ አሰገደች ሁሎችም በጋራ /የመረረ ለቅሶ ያለቅሳሉ/
ትዕይንት ሁለት
/መጋረጃ ሲከፈት ሶስና ዳዊት አቤል እና ወ/ሮ አሰገደች የሀዘን ልብስ ለብሰው ይታያሉ /

ወ/ሮ አሰገደች ፡-ልጆቼ የእሳቴን አደራ እወጣለሁ ጥሩ አድርጌ እንከባከባችኋለሁ አትዘኑ
ሶስና፡-እናቴን በሞት ተነጠኩኝ እናቴን መቼ ነው የማገኛት /እያለቀሰች/
ዳዊት፡-ሶስና አይዞሽ አትዘኝ እናታችን ከዚህ መከራ ከበዛበት ዓለም ደስታ ወደ ሚገኝበት ዓለም ነው የሔደችው ከዚህ በኋላ ማልቀስ አይገባም
አቤል፡-ሶስና ለምን ታለቅሻለሽ አይዟችሁ የኛ ሀብት ለሌላም ይሆናል እንኳን ለእናንተ
ወ/ሮ አሰገደች ፡-እውነቱን ነው አቤል ለማንኘውም እዚህ ከመጣን ሳምንት ሆኖናል ወደ ቤት እንሂድ በሉ ሶሲ ዳዊት እየመጣን እንጠይቃኃለን አቤል ተነስ እንሂድ
አቤል፡,-እሽ /ተያይዘው ይወጣሉ/
ዳዊት፡-ሶስና ከዚህበኋላ እኛ መበርታት አለብን እናታችን ነፍሷን ይማረውና ነገር ሁሉ ለበጎ ነው ።አሁንም እናታችን ብትለየንም እግዚአብሔር አይለየንም አይተወንም
ሶስና፡-ታውቃለህ ወንድሜ እናታችን ስለ እኛ ነበር የምትኖረው እናም እኔ ህልሜ ትልቅ ሰው ሆኘ እናቴን አሳልፌላት ማየት ነበር ግን በአቋራጭ እናቴን ሞት ወሰደብኝ/ታለቅሳለች/
ዳዊት፡-ሶስና ከዚህ በኋላ አትዘኝ አላልኩሽም በይ ቤተ ክርስቲያን ደርሰን እንምጣ ተነሽ እኔንም ምሪኝ/ከተቀመጠበት ተነስቶ/
ሶስና፡-/እንበዋን እየጠራረገች /እሽ--/ተነስተው እየሄዱ ማርያም ሀዘነ ልቦና የሚለውን እየዘመሩ ይሄዳሉ/
ትዕይንት ሶስት
መጋረጃ ሲከፈት ወ/ሮ አሰገደች እና አቤል ቁጭ ብለው እየተነጋገሩ ይታያሉ
ወ/ሮ አሰገደች ፡-አቤል ምልልሱ ገደለኝ በሳምንት ሁለት ጊዜ ከነዚያ ልጆች እየተመላለስኩ ምን ላድርግ ምን ይሻለኛል?
አቤል ፡-እኔ አንችን ከዚያ እየተንከለከልሽ ሲደክምሽ ማየት አልፈልግም ከዚህ በኋላ እኔ እየሄድኩ እጠይቃቸዋለሁ

ወ/ሮ አሰገደች ፡-የለም አንተማ ህጻን ነህ ምልልሱን አትችለውም እነሱ መጥተው ከእኛ ጋር ቢሆኑ ምን ትላለህ?
አቤል፡-ኧረ እናቴ ተሳሳትሽ ከዚህ የሚመጡ በምን ሒሳብ ነው ታውቂያለሽ እሳትሽ ስትሞት ልጆቼን አደራ ያለችሽ ይመስኛለል ግማሹን ሀብት እንድታወርሻቸው ነው።።
ወ/ሮ አሰገደች ፡-ኧረ ተው ልጄ
አቤል ፡-እንግዲያ እንደዛማ ባይሆን ኑሮ ጠንክራችሁ ስሩ ከሰው ምንም አትፈልጉ ትላቸው ነበር
ወ/ሮ አሰገደች ፡-ነው ብለህ ያለ ነገር እጄን ይዛ አደራ አላለችኝም
አቤል፡-እየውልሽ እናቴ እነዚያን ልጆች እስከ መቼ ነው የምታግዣቸው መቼ ወረተውን ሊከፍሉሽ ነው ዳዊት እንደው ዓይኑ ደርጋማ ነው ሶስናም ትምህርቷን አቋርጣለች በእናቷ ሞት ምክንያት ከዚህ በኋላ አትልፊ እናቴ
ወ/ሮ አሰገደች ፡-እና ምን ልበላቸው ልጄ መቼም ልጄ አቤል የልጅ አዋቂ ነህ ይህ ሁሉ አደራ ለሰበብ አልመሰለኝም ነበር
አቤል፡-ከዚህ በኋላ የቀን ስራም ሰራታችሁ ቢሆን እራሳችሁን አስተዳድሩ በያቸው ከዚያ እንደብሻቸው እሽ እማ
ወ/ሮ አሰገደች ፡-እሽ ለእነሱ ለእነሱ እያልኩ አሁንማ ለአንተ ያከማቸውትን አጠፈውት ቢልላቸውማ ኑሮ እናታቸው አትሞትም ር በል አሁኑኑ ሄጄ ልሰናባቸው /ትወጣለች/
አቤል፡-በይ እሽ ተሎ ተመለሽ --------ይገርማል እኮ ሰርተው አይበሉም እንደውሻ የእኛን እጅ የሚያዩ ---ከዚያው ይቆራመድ /ይወጣል/ መጋረጃ ይዘጋል

ትዕይንት አራት

/መጋረጃ ሲከፈት ገብረ ጻድቅና ወለተ ማርያም ተቀምጠው ይታያሉ/
ወ/ማርያም፡-እግዚአብሔርን ብንለምን ልጅ አልሰጠንም ሃብታችን ለማን ልናወርሰው ነው እኔስ ግራ ገባኝ
ገ/ጻድቅ፡-እባክሽ አትዘኝ የሚሰጥም የሚነሳም እግዚአብሔር ነው ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው እግዚአብሔር እያማረርሽ እኮ ነው ተይ እንጅ

ወ/ማርያም፡-እሱማ እግዚአብሔር ያውቃል እንዲህ ቁጭ ስንል የሚያነጋግረን ቢኖር ብየ ነው እኮ ቢሆን ጥሩ ነበር

ገ/ጻድቅ፡-እሱን ተይውና የንስሐ አባታችን ሊመጡ አይደል ተዘጋጅ /አባ ይገባሉ/

አባ፡-አንደምን ዋላችህ ልጆች

ወ/ማርያምና ገ/ጻድቅ/በጋራ/፡-እግዚአብሔር ይመስገን አባ እንደምን ዋሉ /ይሳለማሉ/

ወ/ማርያም፡-ከዚህ ላይ ይቀመጡ

አባ፡-እሽ ልጄ /ይቀመጣሉ/

ገ/ጻድቅ፡-አባ ይች እህቴ እግዚአብሔር ልጅ ካልሰጠኝ ብላ በጣም አዝናለች

አባ፡-ወለተ ማርያም በዚህ ጉዳይ አትጨነቂ እግዚአብሔር ያዘጋጀውሰው ይኖራል ይልቅስ የልባችሁን መሻት ለእግዚአብሔር አቅርቡ ልጆቼ

መ/ማርያም፡-እኔኮ አባ የሚያነጋግረን ቢኖር ብየ ነው

አባ፡-እንግዲያውስ የድሀ ልጅ ብታገኙ አሳደጉ ለነፍስም ለሥጋም ይጠቅማቹኃል ምን ትላላችሁ

ገ/ጻድቅ፡-አባ ጥሩ ሀሳብ ነው እኔም አስቤው ነበር

አባ፡-በሉ እኔም ልሂድ እየመጠሁ እጠይቃቹኃለሁ/ከተመጡበት በመነሳት/

ወ/ማርያም፡-ይበሉ አባሰላም ይዋሉ/አባ ይወጣሉ/

ገ/ጻድቅ፡-በይ እኛም ቤተ ክርስቲያን ደርሰን እንምጣ

ወ/ማርያም፡-እሽ እንሂድ/ተየይዘው ይወጣሉ/ መጋረጃ ይዘጋል

ትዕይንት አምስት

/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊትና ሶስና ተቀምጠው ይታያሉ/

ሶስና፡-አክስታችን በዚህ ሳምንት ቀረች እርሷ ደግሞ ምን ሆና ይሆን

ዳዊት፡-ምንም አትሆንም መመላለሱ ጠንቶባት ይሆናል

ሶስና፡-ዳዊት ከዚህ በኋላ የቀን ስራ ብሰራ ምን ትላለህ

ዳዊት፡-የቀን ስራ ---አስጨነኩሽ አይደል ሶስና ምነው እናቴ ባንች ምትክ እኔ በሞትኩ ነበር እጎቴን ሁሌ እያሳዘንኩ መኖሬ አስጨንቆኛል እማ ---እማ --/ምርር ብሎ በማልቀስ/
ሶስና፡-ለምን ታለቅሳለህ የቀን ስራ ልስራ ማለት ያስለቅሳል እንዴ /ወ.ሮ አሰገደች ትገባለች/
ወ/ሮ አሰገደች፡-ከዚህ ቤት እንዴት ዋላችህ
ሶስና፡-እግዚያብሔር ይመስገን እንደምን ሰነበትሽ አክስቴ /ከጉልበቷ ደፋ በማለት/
ወ/ሮ አሰገደች፡-ጠላትሽ ይደፋ /ይሳሳማሉ/
ሶስና፡-ግቢ ከዚህ ላይ ተቀመጭ ቁጭ በይ
ዳዊት፡-አክስቴ ደህና ነሽ አቤል ደህና ነው በጣም ናፍቆኛል
ሶስና፡-አክሰቴ በሰላም ነው በጣም ነው የቆየሽው
ወ/ሮ አሰገደች፡-አቅቶኝ እርጅና መጣ መሰለኝ አሁንም የመጠሁት በግድ ነው የምነግራችሁ ነገር ስላለ ነው
ሶስና እና ዳዊት በጋራ፡-ምንድን ነው ንገሪን
ወ/ሮ አሰገደች፡-ከዚህ በኋላ መመላለሱ ስለከበደኝ ሶስናም አድገሻል እየሰራሽኑሪ ለሁለታችሁ አታንሽም ገንዘቤንም ለልጄ ሳላስቀምጥ ጨረስኩት ከዚህ በኋላ በቃኝስልችት አለኝ የእጎቴን አደራ እስከ አሁን ተወጠው በቃኝ
ሶስና፡-በዚህ ሁኔታ እያለን እናቴ ከሞተች ስድሰት ወር አልሞላትም
ወ/ሮ አሰገደች፡-ታዲያ አይሙላት እኔ ሰለቸኝ
ዳዊት፡-አክስቴ እኔ ማየት የተሳነኝ ነኝ ሶስናም መስራት አትችልም ባይሆን ትንሽ ብር ስጭንና የሆነ ነገር ሶስና ተጀምርበታለች
ወ/ሮ አሰገደች፡-በቃህ አንተ እውር ብር ለእናንተ እስከ አሁን ያወጠሁት አነሰና ብር ስጭን ----ወይ ጉድ --ከዚህ በኋላ እንደአሻችሁ ሁኑ/ ትወጣለች/
ዳዊት፡-ምነው አምላኬ ባትፈጥረኝ ኑሮ ከዚህ በኋላ እጎቴ ምንድን ነው የምታደርገው እማ ለምን ሞትሽ እናቴ ብቸኝነት ተሰማን እጎትሽም የዱር

አውሬ ይብላችህ ብላ ተወችን/ምርር ብሎ ያለቅሳል/
ሶስና፡-/እያለቀሰች/አይዞህ ዳዊት እናታችን ነፍሷን ይማርና እንጨት ካለበት ለቅማ እየሸጠች የሰው ልብስ እያጠበች አሳደገችን አሁንም እኔ እነዚህን ስራወችን እሰራለሁ
ዳዊት፡-ለምን ታናሽ እህቴን አሰቃያለሁ አንችኮ እኔ ባልኖር ዘና ብለሽ ትኖሪ ነበር
ሶስና፡-/በመናደድ/ ዳዊት እንደዚህማ አትበል ወንድሜ አይደለህም እንዴ
ዳዊት፡-በቃ እግዚአብሔር በጸሎት እንጠይቀው ቤተ ክርስቲያን ሄደን ተነሽ እንሂድ
ሶስና፡-/እጁን በመያዝ/---/ኃይልን በሚሰጠኝ ሁሉን እችላለሁ የሚለው መዝሙር ይዘመራል/---/ተያይዘው ይወጣሉ/ መጋረጃ ይዘጋል

ትዕይንት ስድስት

/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊትና ሶስና ተኝተው ይታያሉ/

ዳዊት፡-/ተነስቶ/ አምላኬ ሆይ እሳቴን አላሳዝንም ከዚህ ቁጭ ብየ ስለዚህ ወጥቼ እሄዳለሁ አምላኬ በመንገዴ ምራኝ የዓይኔን ብርሀን መልስልኝ ይች ዓለም ምን እንደሆነች ልያት አምላኬ ሆይ ስለናትህ ቅድስት ድንግል ማርያም ብለህ እኔን ኃጢያተኛውን እራራልኝ እየመራህ አንተ ካዘጋጀህው ቦታ አስቀምጠኝ እህቴን ጠብቅልኝ ለእርሷ የሚጠቅማትን ስጣት አሁኑኑ ወጥቼ እሄዳለሁ /ወጥቶ ይሄዳል/
ሶስና፡-/ከተኛችበት ትነሳለች/ ዳዊት --ዳዊት --ወዴት ነህ ዳዊት /ከቤት ውስጥ ትፈልጋለች/-ዳዊት ወዴት ሄድክ እመ ብርሃን ሆይ ወንድሜን ያለበትን አመልክችኝ እናቴን በሞት ተነጠኩ አለኝ የምለው ወንድሜም ጠፋኝ ፈጣሪየ ወዴት ነው ዳዊት ያለው ፈጣሪየ ምነው መከረው በዛብኝ ምን በደልኩህ --አምላኬ ሆይ----/ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች/---መጋረጃ ይዘጋል

ትዕይንት ሰባት

/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊት ይታያል/

ዳዊት፡-/ዓይኑን እምነት እየቀባ/ አምላከ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ እይታየን መልስልኝ አይቼ ልሙት --አምላኬ ሆይ ዓይኔን አብራልኝ ---ዘመኔን ሁሉ ከቤትህ አልለይም በምችለው መጠን በአገልግሎት እጠናለሁ /ዓይኑን እምነት ይቀበዋል ዓይኑም ይበራል/---እ--አይኔ ---አይኔ--/ተደስቶ እየተንቀሳቀሰ/--አይኔ በራ--አይኔ በራ ተመስገን አምላኬ--ተመስገን አምላኬ--ለአንተ ምን ይሳንሀል ምስጋና ይድረስህ ተመስገን አምላኬ / መጋረጃ ይዘጋል/

ትዕይንት ስምንት

/መጋረጃ ሲከፈት ሶስና ትታያለች/

ሶስና፡-/ተንበርክካ እየጸለየች/ አምላኬ መከረው ብቸኝነቱ ፀናብኝ ከዚህ በኋላ እኔም ከዚህ ቤት አልቀመጥም ምክንያቱም ወንድሜን ለመፈለግ እወጣለሁ ስለዚህ አምላኬ በመንገዴ ተከተለኝ ብቸኛ ወንድሜን አገኛው ዘንድ እርዳኝ ወንድሜንም ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀው /ትነሳለች/--አሁኑኑ እሄዳለሁ/ወጥታ ትሄዳለች መጋረጃ ይዘጋል/

ትዕይንት ዘጠኝ

/መጋረጃ ሲከፈት ገ/ጻድቅ እና ወ/ማርያም ተቀምጠው ይታያሉ/

ወ/ማርያም፡-ዛሬ በጣም ስራ ስለበዛብኝ እንዴት እንደደከመኝ አትጠይቀኝ ድክም ብሎኛል

ገ/ጻድቅ፡-እኔም እንዳላግዝሽ ስራ ስለሚበዛብኝ ላግዝሽ አልቻልኩም ወ/ማርያም አይዞሽ ደግሞ እኮ ተሎ የሚደክምሽ ስለ ልጅ ስለምታስቢ ነው ስሚኝማ እኅቴ ሰራተኛ ብንቀጥር ምን ትያለሽ

ወ/ማርያም፡-ኧረ እኔም አጠያየቁ ጨንቆኝ ነው እንጅ ልጠይቅህ ነበር ልጅ አላሳድግ የምሰረው የለኝ እኔ ምን ልስራ እያልኩ ሰውም ይስቅብኛል ብየ ነው አሁን ግን በአንተ ስለመጣ ደስ ብሎኛል

ገ/ጻድቅ፡-በቃ ከዚህ በኋላ ደግ የሆነች ልጅ ይስጠን እንጅ ግማሹ ሀብታችንንም እንሰጣታለን ብቻ መልካም ሰው ትሁን በይ እኔ ፈልጌ ልምጣ/ተነስቶ ወጥቶ ይሄዳል/

ወ/ማርያም፡-ከዚህ በኋላ አምላኬ ስራ የሚያግዘኝ ከተገኘልኝ ደስ ብሎኝ እኖራለሁ እንደ ልጅም አድርጌ አያታለሁ ጥሩ ልጅ ከሆነች ደግሞ ቅብጥ አድርጌ እድራታለሁ /ወጥታ ትሄዳለች/

ትዕይንት አስር

/መጋረጃ ሲከፈት ሶስና ስትንከራተት ትታያለች/

ሶስና፡-አቀበት ቁልቁለቱን ወጣሁ ወረድኩ ወደ ምሥራቅ ወደ ምዕራብ ወደ ደቡብ ወደ ሰሜን ወደ አራቱም አቅጣጫ ተጓስኩኝ ላገኘው አልቻልኩም አምላኬ ለምን እንደምንከራተት ታውቃለህና አንተ አሳካልኝ አምላኬ ሆይ ወንድሜን ማግኘት እሻለሁ /ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች ገ/ጻዲቅ ይገባል /

ገ/ጻድቅ፡-/ሶስና እያለቀሰች ይመለከታል / ልጄ ምን ሆነሽ ነው

ሶስና፡-በድህነት ቤት እናታችን እኔንና ወንድሜን አሳደገች ሳናስደስታት ሞተችብን ከወራት በኋላ ደግሞ ወንድሜ ጠፋብኝ አሁን እርሱን ፍለጋ እንከራተታለሁ /እያለቀሰች/

ገ/ጻድቅ፡-ልጄ እና ወደ ቤትሽ መመለስ ትፈልጊያለሽ

ሶስና፡-አልፈልግም ወንደሜ ከሌለበት ቤት መኖር ብመለስ እንኳን የምበለው የለኝም ከቻልክ ከሰው ቤት አስገባኝ

ገ/ጻድቅ፡-ከሰው ቤት /እያዘነ ቆም ብሎ ያስብና/ በቃ ልጄ ከእኔ ጋር ትኖሪያለሽ አሁን ተነሽ እንሂድ ልጄ

ሶስና፡-እሽ /ተያይዘው ይወጣሉ/

ትዕይንት አስራ አንድ

/መጋረጃ ሲከፈት ወ/ማርያም ተቀምጣ ትታያለች/

ወ/ማርያም፡-ወንድሜ ገ/ጻድቅ ቀረ ምን ነካው እኔን ለማስደሰት ብሎ ሄዶ ምን ገጠመው /ገ/ጻድቅ እና ሶስና ይገባሉ/

ገ/ጻድቅ፡-ወ/ማርያም ደስ ይበልሽ ይህችን ልጅ አመጣሁልሽ ከዚህ በኋላ ተባብራቹህ እየሰራችህ ኑሩ እሽ

ወ/ማርያም፡-መጣችህ በሉ ቁጭ በሉ ምግብ ብሉ /ይቀመጣሉ የሚበላ ምግብ ታቀርብላቸዋለች እርሷም አብራ ትቀመጣለችጸሎት አድርገው ይመገባሉ/

ገ/ጻድቅ፡-ስምሽማን ነው?
ሶስና፡-ሶስና እባላለሁ
ወ/ማርያም፡-ሶስና ከዚህ በኋላ እኔና አንች እንደ እናትና እንደ ልጅ ነው የምንኖረው እሽ
ሶስና፡-እሽ እናቴ እናንተም ቢሆን በነፃነት አዝዙኝ
ገ/ጻድቅ፡-ተመስገን አምላኬ ተመስገን ወ/ማርያም በይ ቤተ ክርስቲያን ደረስ ብለን እንምጣ
ወ/ማርያም፡-በል እሽ ሶስና የሚሆንልሽን ስሪ ከደከመሽ ደግሞ ስመለስ በጋራ እንሰረዋለን ነገ አብረሽን ትሄጃለሽ እሽ
ሶስና፡-እሽ /ተያይዘው ይወጣሉ/
ሶስና፡-ተመስገን አንተ ከጎኔ ስላለህ ከነዚህ ሰወች ጣልከኝ ተመስገን -- ተመስገን ተመስገን/ትወጣለች/

ትዕይንት አስራ ሁለት

/መጋረጃ ሲከፈት ወ/ማርያም ገ/ጻድቅ ተቀምጠው ይታያሉ /
ወ/ማርያም፡-ይችን ልጅ ቁም ነገር አላት እግዚአብሔር ይባርካት
ገ/ጻድቅ፡-ከሁሉም በላይ ትህትነዋ እጅግ ልዩ ነው ሶስና ሶስና
ሶስና፡-አቤት አባቴ ጠራኸኝ እንዴ
ገ/ጻድቅ፡-አዎ ልጄ እጅግ የምትገርሚ ልጅ ነሽ አንችን የወለደች ያሳደገች እናት ምን ዓይነት የታደለች ናት ከዚህ በኋላ ልጄ ሶስና ሳይሆን ትህትና እንልሻለን
ወ/ማርያም፡-የሚደንቅ ስም ነው አዎ ልጄ አይዞሽ ሀብታችንን ሁሉ እናወርስሻለን አንች ብቻ በርች እሽ ልጄ
ገ/ጻድቅ፡-በሉ 11 ስዓት ስለደረሰ ቤተ ክርስቲያን ደርሰን እንምጣ
ወ/ማርያም እና ሶስና ፡-/በጋራ / እሽ /ተያይዘው ይወጣሉ

ትዕይንት አስራ ሶስት

/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊት ሻንጣ ይዞ እየተጓዘ ይታያል/
ዳዊት፡-በከተማ ውስጥ ነው የምኖረው ምን አስጨነቀኝ እግዚአብሔር ለእኔ መልካምን ነገር አድርጎልኛል ዓይኔን አበራልኝ ትምህርቴን

አስጨረሰኝ ተመርቄ አሁን የባንክ ሰራተኛ ሆኛለሁ ከቤቱም አልጠፈውም ታዲያ ምን ያስጨንቀኛል /ወ/ማርያም ገ/ጻድቅ እና ሶስና ይገባሉ/
ገ/ጻድቅ፡-እንደምን ዋልክ ልጄ
ዳዊት፡-እግዚያብሔር ይመስገን እንደምን ዋላችሁ / ሰላምታ ይለዋወጣሉ/
ገ/ጻድቅ፡-ምነው እንግዳ ትመስላለህ
ዳዊት፡-አዎ ለዚህ አካባቢ እንግዳ ነኝ
ወ/ማርያም፡-ታዲያ በምን ምክንያት መጣህ
ዳዊት፡-ስራ ተቀጥሬ ለስራ ነው የመጣሁት እናም ዶርም ፈልጌ ነበር የምታውቁት ይኖራል
ገ/ጻድቅ፡-ከእኛ አለ ትከራያለህ? እንሂድ በሉ /ተያይዘው ይወጣሉ/
ትዕይንት አስራ አራት
/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊት ወ/ማርያም ገ/ጻድቅ እና ሶስና ይታያሉ/
ገ/ጻድቅ፡-ልጄ ስምህ ግሩም ነው ያለከኝ
ዳዊት፡-አዎ አባቴ
ገ/ጻድቅ፡- ግሩም---ግሩም ---ግሩም ነው ይገርማል
ወ/ማርያም፡-ግሩም ፀባይህ ገና በሳምንት ውስጥ ተመችቶኛል እንደ ትህትና ነው የምትመስል
ዳዊት፡-ትህትና ግን በዚህ ሳምንት በአልሞላ ውው-ግሩም ነው ይገርማ
ወ/ማርያም፡-ግሩም ፀባይህ ገና በሳምንት ውስጥ ተመችቶኛል እንደ ትህት ናነው የምትመስል
ዳዊት፡ትህትና ግን በዚህ ሳምንት በአልሞላ ውስጥ ሳያት ሁሉን ነገር እንደ ርሷ መሆንን ተመኘው ትህትነዋ ደግነቷ ታዛዥነቷ ሰው አክባሪነቷ እናትና አባት አክባሪነቷ---ሁሉ ነገ ርበጣም ደስ ይላል
ሶስና፡-ግሩም ተው እንደዚህ አትበል
ወ/ማርም፡-በይ ሶስና አባ ነገ ስለሚመጡ እንዘጋጅ /ሶስና እና ወ/ማርያም ይወጣሉ/

ገ/ጻዲቅ፡-ልጄ ግሩም አድምጠኝ ደስ ብለህኛል እናም ልጆችንን ሶስናን ብታገባት ምን ትላለህ ቤታችንን ንብረታችንንም ውረሱ ልጄ
ዳዊት፡-ይሻላል ብለህ ነው አንተ ካልክ እሽ
ገ/ጻዲቅ፡-ተመስገን--ተመስገን አምላኬ ልጄ እንደማታሳፈረኝ አውቄ ነበር /አባይገባሉ/
አባ፡-እንደምን ዋላቹህ ልጆቼ
ገ/ጻዲቅ፡-እግዚያብሔር ይመስገን አባ /ይሳለማሉ/
ገ/ጻድቅ፡-ቆይ ልጥራቸው ወለተ ማርያም አባ መጥተዋል /ሶስና እና ወ/ማርያም ይገባሉ/
ወ/ማርያም፡-አባ እንኳን ደህና መጡ/ይሳለማሉ/
አባ፡- ትህትና እንዴት ነሽ ደግሞ ትልቅ ልጅ ሆነሻል
ገ/ጻድቅ፡-እርሷን የሰጠን አምላክ ይመስገን
ወ/ማርያም፡-ትህትና የሚበላ የሚጠጣ ነገር ለአባ አምጭላቸው
አባ፡-ልጄ ተቀመጭ ምንም አላደርግም ነይ ተቀመጭ
ሶስና፡-እሽ
ገ/ጻድቅ፡-አባ ያስጠረዎት ይህ ልጅ ግሩም ይባላል እናም ትህትናን ላጋበው እና ሀብት ንብረቴን ላወርሳቸው ፈልጌ ነበር ምን ይላሉ
አባ፡-ይህማ የተቀደሰ ሀሳብ ነው ሰው በትዳር ተወስኖ ይኖር ዘንድ ግድ ነው እግዚአብሔር አዟልና እነሱ ከተስማሙበት ጥሩ ሀሳብ ነው
ገ/ጻድቅ፡-ልጄ ትህትና አታሳፍረኝም ግሩምን ነግሬው በሀሳቡ ተስማምቷል ትህትና አንችስ ምን ትያለሽ
ሶስና፡-የእናንተን ሀሳብ አልቃወምም
ወ/ማርያም፡-ልጄ እግዚአብሔር ይባርክሽ
አባ፡-በሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ሰርጉን ደግሱና በቤተ ክርስቲያን ስርዓት ይዳራሉ አሁን የምሄድበት ስላለ ደረስ ብየ ልመለስ
ገ/ጻድቅ፡- እንሸኘወት አባ /ሁላቸውም ተያይዘው ይወጣሉ/
ትዕይንት አስራ አምስት
/መጋረጃ ሲከፈት ዳዊትና ሶስና ተቀምጠው ይታያሉ/

ዳዊት፡-ይህን ያህል አብረን ስንኖር ስለ አንች አውርተሸኝ አታውቂም እኔም ስለ እራሴ አውርቸሽ አላውቅም
ሶስና፡-አይ ግሩም ሰርጋችን 3 ቀን ብቻ ነው የቀረው ታዲያ ከዚህ በኋላ ምን ይሰራልናል ከ 3 ቀን በኃላ እናወራለን
ዳዊት፡-ትህትና ከኔ የምትደብቂው ነገር አለሽ እንዴ / በመናደድ /
ሶስና፡-አንተን ላስቀይም አልፈልግም ስለ እኔ ህይወት ላውራህ አድምጠኝ እነዚህ ሰዎች እናቴ እና አባቴ አይድሉም አሳዳጊየ እንጅ
ዳዊት፡-እንዴት
ሶስና፡-እየውልህ ግሩም እናቴ ያለ አባት ከወንድሜ ጋር አሳደገችኝ ከዚህ በኋላ እናታችን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች አክስታችንም ገንዘብ እየሰጠች ለትንሽ ወራት ቆየን ከዚያም አክስታችን እናንተን ማየት አልፈልግም አለችን ከዚያም ጨለማ ዋጠን
ዳዊት፡-ከዚያስ /ለስለስ ባለ ድምጥ/
ሶስና፡-ከዚያማ ወንድሜ ከተኛበት ጠፋኝ እርሱን ፍለጋ ተንከራተትኩኝ አቀበት ቁልቁለት ወጠሁ ወረድኩ ላገኘው አልቻልኩም ----ሌላ አማራጭ የለኝም ነበርና ከሰው ቤት ገበው ማለቴ እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር ጣለልኝ
ዳዊት፡-የወንድምሽ ስም ማን ይባላል? ምን አይነት ነበር እባክሽ ትህትና ተረጋግተሽ ንገሪኝ
ሶስና፡-ከዚህ ውጭ ምን ልንገርህ
ዳዊት፡-የእኔ እና የአንች ህይዎት ተመሳሳይ ስለሆነብኝ
ሶስና፡-ወንድሜ አይነ ስውር ዳዊት ይባል ነበር እኔ ደግሞ ሶስና እባል ነበር
ዳዊት፡-ሶስና እኅቴ እ--ኅ--ቴ እኔ ወንድምሽ ዳዊት ነኝ /ተነስተው ተቃቅፈው ይላቀሳሉ/- ገብረ ጻድቅ ይገባሉ/
ገብረ ጻድቅ፡-/በመናደድ/ ምን ሆናችሁነው እንደሱ ሆናችሁ ተቃቅፋችሁ የምታለቅሱ
ሶስና፡-አባቴ ይህ ልጅ ወንድሜ ዳዊት ነው

ወ/ማርያም፡-እንዴት ሊሆን ይችላል አይነ ስውር አይደል እንዴ ወንድምሽ በዚያ ላይ ደግሞ ይሄ ግሩም ነው
ገ/ጻድቅ፡- ተመስገን --ተመስገን አምላኬ ተመስገን
ዳዊት፡-ይኼው እላችሁ እግዚአብሔር አይኔን አብራልኝ ብየ ለመንኩት እይታየንም መለሰልኝ ደግሞም ሶስናን ሳላያት እንዳልሞት ብየ ለመንኩት ይኼው አገናኘን ተመስገን ---ተመስገን --አምላኬ
አባ፡- እግዚአብሔር ስራው ድንቅ ነው አያችሁ ልጆቼ ለ10 ዓመታት ተለያይታችሁ ቆይታችሁ እግዚአብሔር ግን በስላም በነዚህ ደግ ሰዎች ቤት ተገናኛችሁ በሉ ልጆቼ በእድሜ ዘመናችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን አገልግሉ በሉ እናንተም ወ/ማርያም ገ/ጻድቅ የእናንተ ደግነት እነዚህን ልጆች አገናኛቸው በሉ ልጆቼ ተነሱ በአንድነት እግዚአብሔርን እናመስግነው።

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን/የሚለውን መዝሙር በጋራ ይዘምራሉ/
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር
በወለተ ሥላሴ
በደ/ነ/ገ/እማ ሸንኮሮ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት ኪነ-ጥበብ ክፍል
የተዘጋጀ ፲፱-፲ -፳፻፲፩ ዓ.ም